# በቤተ-ክርስቲያን ካባ ስወር የፖለቲካ ደባ!!!

## በደቡብ አፍሪካ የኦረቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች ጆበርግ

## በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ አሜን!!!

*kedusghebriel@gmail.com*

«ነገር ግን ሐሰተኞች ነቢያት በሕዝቡ ዘንድ ነበሩ በእነሱም ጠንቅ የእዉነት መንገድ ይሰደባል:: ሐቅ/ጴጥ በም2:3

***የእግዚአብሔር የሆነ እውነትን ይናገራል ( የሀሰተኞች ግን... የአባታችሁን ፍላጎት ለመፈጸም ትሻላችሁ እርሱም ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነው::) ዩሐ 8:44***

መጀመሪያ በአማናዊቷ ቤተ ክርስቲያን ፈተና አሳሳቢነት በማዘን ወያኔ በቤተ-ክርስቲያናችን ዉስጥ የራሱን ሰዎች አሰማርቶ እየፈጸመ ያለዉ መጠነ ሰፊ ጥፋትና የህገ ቤተ-ክርስቲያናችን አለመከበር ሁኔታ እንደ ቤተ ክርስቲያኗ ልጅነታችን ተሰምቶን ጉዳዩ የትጋር እንደሆነ እየጠቆምን ዝም ብለን ካየን ግን ነገሩ አቅጣጫዉን ቀይሮ እንዳያልፍ በማሰብ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ከፖለቲካ ምሺግነት ለይተን አጋጣሚዉን ተጠቅመዉ የተፈጠረዉን ችግር ሐይኖታዊ በማስመሰል በዉል የማያዉቀዉን ምእመናን በተለይ ወጣቱን ወደ ሌላ አቅጣጫ ለማስቀየር ከሚፈጠሩ መናፍቃንና ከመሳሰሉት ችግሮች እንድንጠነቀቅ ባለፈዉ በኢትዮጵያና በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች ለሚገኙ ወገኖቻችን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊያንና ለሚመለከታቸዉ አካላትም በማስተላለፍ መድሐኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የቤተ-ክርስቲያን ሰላም ይመልስልንና የአባቶቻችንና የምእመናንንም እንባ ያብስልን ዘንድ የእመቤታችን ጾመ ፍልሰታ በመጾምና በመጸለይእንድንተጋም በትህትና መጠቆማችን እናስታዉሳለን::

ከሱባኤ በኋላ ማንኛዉም የእምነታችን ተከታይ አዉቆ እንዲጠነቀቅ እኛ ባለንበት በሳዉዝ አፍሪካ ወያኔ ለራሱ አላማ ባሳፋሪ ሁኔታ ያለ ህገ ቤተ ክርስቲያን ያስቀመጣቸዉን ቤተ ክርስቲያናችንና ሊቃዉንት አባቶቻችን ከጥዋቱ የማያዉቋቸዉን የደርግ ወታደር አስማማዉ የወያኔዉ የዉሸት ጳጳስ አቡን ያእቆብ በሳዉስ አፍሪካ ከኢባሲዉ ጋራ በመሆን እየፈጸሙት ያለዉን እኩይ ተግባር እዉነተኛ ታሪክ ከነማስረጃዉ የምንገልጽ መሆኑን በቀጣዮ መሰናበታችን በማስታዎስ ይህን ጽሑፋችን ለማንበብ ላጋጠማችሁ በኢትዮጵያና በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች ለምትገኙ ከላይ ጀምሮ እስከ ታች በየደረጃችሁ ምእመናን ወገኖቻችን በሙሉ ከእግዚአብሐር አብ ከጌታችንም ከኢየሱስ ክርሰቶስ ጸጋና ምህረት ሰላምም ይሁንላችሁ 2ኛ ጢሞ 1:2 ::

- **የደርግ ወታደር የነበረዉ 10 አለቃ አስማማዉ/አባ ያእቆብ /ምን አይነት ሰዉ ነበሩ? ከየትኛዉ ብረጌድ ስንተኛ ሻበል ስንተኛ ክፍለ ጦር ስተኛ ኮር ?**
- **ደርግ ከወደቀ በኋላ የት ነበሩ ?ወደ ቤተ ክርስቲያን መቸ ቀረቡ የዲቁና ማዕርግ መች ተቀበሉ? በማን?**
- **በዚህ የሚገኘውን የኢትዮ- ኮሚዩኒቲ አንድነት እንዳይኖረው ምን ታቅዶ ነበር?**

አበዉ ስለ እዉነት ተናግረዋል እንዲህ ሲሉ «ትዘገያለች እንጅ አትጠፋም » በመጽሐፍ ብዙዎች የቀናውን ነገር ወደ ጥመት እንደሚመልሱት እኔም ዛሬ ይህንን ምስጢር መርምሬ አዉቄዋለሁ ምሳ 40:34 እንደተባለ <u>በደቡብ አፍሪካ የኢትዮጵያ ኦርቶዶስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስቲያን እምነት ተከታዮች</u> ባወጣነዉ መግለጫ ላይ ቁስላቸዉ የተነካ ይመለከተናል ባዮች « በስድብ የቤተ-ክርስቲያን ችግር አይፈታም » በሚል ርእስ በዉስጣቸዉ ተንኮል አዝለዉ በቤተ ክርስቲያናቸንና በሐይማኖታችን ካባ ስዉር የፖለቲካ ደባቸዉን አሳይተዉናል/አስነብበዉናል/ እንዲያዉም ያልወከሏቸዉን ምዕመናን ወክለዋልም ብለዋል :: በዲዩትሮኒካል Deyoerocanyonical መጽሐፍ ቅዱሳችን መጽሐፈ ጥበብ 9:4 ላይ «የሚኖች አሳባቸዉ ፈራሽ መንገዳቸዉም ጎጻጉጽ ነዉና እግዚአብሐር የሚወደዉን አስቦ የሚያውቅ ማን ነዉ?» የሚፈርስ ሥጋ ነፍስን ያሸንፋታል: ያፈዛታል <u>ምድራዊ ስጋ ልብን ያደነቁራል</u> ተብሎ ተጽፏልና እነዚህ በዉስጣቸዉ ክርስቶስን ያላስገቡ ክርስቲያኖች ነን የሚሉ በሀሰት እዉነትን የሚቀብሩ :በትቢትና በተንኮል ተረግዘዉ በአመጻ የተወለዱ ልቡናቸዉን አደንቁረዉ የማይሰሙ በመሆናቸዉ አበዉ ደንቆሮ የሰማለት ያብዳል እዲሉ አባቶቻችን እነአባ ገብረመድህን /አባ ጳዉሎስና/ 10 አለቃ አስማመዉ /አባ ያዕቆብ/ ተነኩብን ብለዉ የይስሙላ መሸፋፈኛ መልሳቸዉን በተለመደ ቅጥፈታቸዉ ጽፈዋል ::

አወ ታዲያ በመጽሐፍ ቅዱስ «ከእሾህ ወይን ከኩርንችትስ በለስ ይለቀማልን »? ማቴ 7 16-19 ተብሎ ተጽፏልና አባታቸዉ ገና በክርስቶስ ያልተጠራ ሳዉል በመሆኑ ግብሩም በቤተ-ክርስቲያን አዉደ ምህረት ደም ማፍሰስ: መግደል : ንጹሃን ታዳጊ ወጣቶች ተማሪዎችን/ ከቅጽረ ቤተ-ክርስቲያን ግቢ አስወጥቶ ለሞት ሲሳይ ማድረግ : በሐይማኖት ተሸፍኖ ፖለቲካ ማራመድ የዘወትር ተግባራቸዉ በመሆኑ እኛም ተከታዮቻቸዉን ከስራቸዉና ከሱም ፍሬዎች ምንም አይጠበቅባቸዉም ማቴ 7 15

መቸም በማስመሰል ምእመናንን በማሳሳታቸው ከእዉነት ፍርድ የማያመልጡ መሆኑ አይቀሬ ነዉ ዳሩ ግን ለጊዜዉም ቢሆን ማንነታቸውን አብዛኛዉ ሕዝብ ስለሚያዉቀዉና ማንነታቸው በስራቸው ስለተጋለጠ በሐይማኖታችንና በሀገራችን ጥፋት :በምሁራን የሀገራችንና የሀይማኖታችን ብርቅየ ልጆች

እንደነ ብጹዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ: እንደነ ብጹዕ አቡነ መርቆ ክርስቶስ አለቃ ኤሌዉ ታምሩ መላከ ሰላም ዳኛቸዉ :በቁጥር ብዙዎች አባቶቻችን ሊቃዉንተ ቤተ ክርስቲያን መነኮሳት ካህናትና ምዕመናን እንባ የሚቀልዱ በመሆናቸው እኛ ግን ቀኑ እስኪደርስ በሃሰታቸው አንጠፋም የእስራኤል ቅዱስ የክብር ንጉሥ እግዚአብሔር ይጠበቀናልና :: ሐዋርያዉ ቅ/ጴጥ በም2:3 «ነገር ግን ሐሰተኞች ነቢያት በሕዝቡ ዘንድ ነበሩ በእነሱም ጠንቅ የእዉነት መንገድ ይሰደባል:ገንዘብን በመመኘት በተፈጠረ ነገር ይረቡባችኋል ፍርዳቸዉም ከጥንት ጀምሮ አይዘገይም ጥፋታቸዉ አያንቀላፋም» እንዳለ እነሱም ዛሬም የእዉነት መንገድ እንዲጠፋ ለፍቅረ ንዋይ የተገዙ በመሆናቸዉ በገዥው መንግስትና በአባ ጳዉሎስ /አባ ገብረመድህን / የተመረጡ ካድሬዎች በገንዘብ ምኞትና በሹመት ፍላጎት በተፈጠረ ነገር በሀሰት የሚሰሩ በመሆናቸዉ ባወጣነዉ መግለጫ ላይ በማጣመም በሰጡት የማስተባበያ መልስ ጽሑፋቸዉ ግብራቸዉ ከዲያብሎስ በመሆኑ ጠብና ጥላቻን ዘርተዉ መለያየትን የሚጭዱ: ከእዉነትም ተጣልተዉ ሀሰትን የሚናፍቁ በዉስጣቸዉ የወያኔ መንግስትና የአባ ገብረ መድህንን አላማ ሰንቀዉ እዉነተኛዉን መንገዳችንን መጽሐፍ ቅዱሱን እንደተመቻቸዉ የሥጋ ሀሳባቸዉ በመተርጎም በተለመደዉ የቃላት ማጣመምና መቀየር ተንኮላቸው የሚያወሩ እስካሁን ጸጸት ተሰምቷቸዉ ንስሀ ያልገቡ አመጸኞች አለን? ሲሉ በጻፉት መልሰ:: በሚሉት ላይ አስተያት ሰጥተን ወደ ማጠቃለያ ጉዳያችን እናልፋለን::

1/ ጸሐፊዎቹ በመጀመሪያዉ አንቀጻቸዉ ላይ ቤተ-ክርስቲያን ከዉጭም ከዉስጥም የተነሱ ፈተናዎችን ስትጋፈጥ እንደቆየች ገልጸዉ ሰሞኑን በአለቃቸዉ በአባ ገብረ መድህን/አባ ጳዉሎስ/ የተፈጠረዉ ችግር የዚሁ ቅጣይ ነዉ ብለዋል ::

እዉነት ነዉ ::ይህን አንቀጽ እኛም እንቀበለዋለን ::ምክንያቱም አባ ገብረ መድህን በቤተ-ክርስቲያናችን ላይ 17 ዓመት መፈንቅለ ሲኖዶስ ካደረጉበት ጊዜ ጀምሮ ያጠፉት መጠነ ሰፊ ጥፋት ከነጉዲትና ከነግራኝ :ከካቶሊካዉያኑና ከሚሲዮናዉያኑ በይዘቱ የተለየ አሳፋሪ ተግባር በመሆኑ ቢበልጥ እንጅ አያንስም :: ምክንያቱም የዉጭ ጠላቶቻችን እራሳቸዉ ላመኑበት እምነትና አላማ ሲሉ ነዉ ያ ጠፉብን ያባ ጳዉሎስ ግን እጅግ በጣም ቢያሳፍርም አንቀጹ እኛንም ያስማማናል ::

በተዋህዶ ለምናምን የቤተ-ክርስቲያን ራስ ኢየሱስ ክርስቶስ በመሆኑ መሰረቷ ባይጠፋም በዘመነ መሳፍንቱና በዘመነ መኳንንቱ ጊዜ የጦር መሳሪያ ወደ ሀገራቸዉ ለማስገባት ሲሉ ከፈንጆች ጋር በሚያደርጉት ግንኙነት ካቶሊካዉያኑና ሚሲዮናዉያኑ የራሳቸዉን ሐይማኖት ለማስፋፋት ሰንቀዉ በመግባት በቤተ-ክርስቲያናችን ላይ መጠነ ሰፊ ችግር አድርሰዋል :: የቤተ-ክርስቲያናችን ቅርስ ከመመዝበርና ከማዉደም ከማቃጠል ባሻገር አስተምሕሮዋንም በመበረዝ በሊቃዉንቱ መካከል ሰርግዉ በመግባት እስካሁን ድርስ ሳይሞት በቤተ- ክርስቲያን ዉስጥ ለዉስጥ ያለዉን የቅባትና የጸጋ ሐይማኖት ዘርተዉ አልፈዋል:: ይሁን እንጅ ለአባቶቻችን ለሊቃዉንቱ ክብር ይግባቸዉና ቤተ ክርስቲያኗን አንድ አድርገዉ አጽንተዉ በመጠበቅ የቤተ- ክርስቲያኗን ጠላቶች አንገታቸዉን አስደፍተዋል ::

**ሌላዉ ደግሞ በዮዲትና በግራኝ** ጊዜ የተፈጠረዉ መጠነ ሰፊ በቤተ-ክርስቲያናችን ላይ ያደረሱት ጥፋት ሲጠቀስ ይህም የራሳቸዉን ሐይማኖት ለማስፋፋት የፈጸሙብን ዘግናኝ የዉጭ ጠላቶቻችን ጥፋት ሲሆን ለተነሱብን ጠላቶች ሁሉ ነገሥታቱ ከሕዝቡ: ካህናቱ ከምእመናኑ በመተባበር በአንድነት መስዋእትነት ከፍለዉ ያለመሳሩያ በፈረንጅ ጥይት እየተቆሉ ለቤተ ክርስቲያናቸዉ ሲሉ የሞቱት ሞተዉ:የተረፉት ቅዱሳን አባቶቻችን ቀሪዉን ጥቂት የማይባል ቅርስና ታሪካችንን:ሐይማኖታችንና ንዋየ ቅድሳታችን ለኛ በቀጥታ አድርሰዉልናል::

**ምቅርቡም ሌላዉ የደርግ ጥፋት ነዉ:-** አብዮታዊዉ ደርግ የቀድሞዉን ስርአት ገርስሶ የቤተ ክርስቲያናችን ባለዉለታ የሆኑትን ብርቅዩ አባት አጼ ኃይለ ሥላሴን ገልብጦ /ገሎ/ ወንበር ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ ጣቱን ቀስሮ ፊቱን ያዞረዉ በዚህችዉ ቤተ ክርስቲያን ላይ ነበር:: የቤተ ክርስቲያነኗን በሮች አዘግቷል : ምእመናኑ ቤተ ክርስቲያን እንዳሄዱ እንዳይጸሙና እናዳይጸልዩ መጠነ ሰፊ መሰናክሎችን አድርጓል::

**<u>ሌላዉ የሚያሳዝነዉና የሚያሳፍረዉ በሀገራችንና በሐይማኖታችን ታሪክ ላይ እንደ አባ ገብረ መድህን የታሪክ ጠባሳ ጥሎ ያለፈዉ ጉዳይ አባቶቻችን አባታቸዉን እንዲገደሉ ለደርግ በፊረማቸዉ አጽድቀዉና አሳልፈዉ የሰጡበት ነዉ:: ታላቁን ሊቅ አባት ብጹዕ ወቅዱስ አባታችን አቡነ ቴዎፍሎስን እንደ አሁኑ የወያኔዉ አባ ገብረ መድኅን ፍቅረ ሲመት /የሹመት ፍቅር/ በተጠናወታቸዉ ሰዎች ምክንያት ፓትርያርኩ ከተሰወሩበት ጠቁመዉ ለሞት ሰለባ አድርገዋቸዋል :: አሁንም በስልጣን ላይ ያለዉ መንግስት ያደረገዉ ይህንኑ ነዉ ለየት የሚያደርገዉ ነገር ፓትርያርክ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ በእግዚአብሔር ቸርነት ከሞት መትረፋቸዉ ነዉ ::</u>**

በአጠቃላይ በቤተ-ክርስቲያናችን ላይ ፈተና አጥልቶባት ቢቆይም የአሁኑን የ17 ዓመቱ የአባ ገብረ መድህን /አባ ጳዉሎስን/ ጥፋት ለየት የሚያደርገዉ

ሀ/ ዕድሜ ለነሱ ወያኔዎች ቅዱስ ፓትርያርኩን ጨምሮ ብጹአን አባቶችን፡ እንዲሁም ሊቃዉንቱ ተሰደው እንደ አባ ገ/መድህን ለፖለቲካ ሳይቆሙ ስደተኛውን ህዝብ በመሰብሰብ በማገልገል ሳይሰለቹ በስደት እንኳን ከክርስቶስ በተሰጣቸዉ ኃላፊነት በዉጭ ቤተ-ክርስቲንን አስፋፍተዉ ምዕመናን ስለጠበቁ መንግስት ለፖለቲካዉ ስላሰጋዉ ምዕመናንን ለመከፋፈል እንደ ወታደር አስማማዉ /አባ ያእቆብ/ ለፖለቲካዉ ከመለመላቸዉ ጥቂት ካድሬዎች ጋር በመሆን ብጹአን አባቶችን ምክር ሳይሰሙ በማስገደድ ወፈገዘቱን መቀባጠሩ በቤተ-ክርስቲያናችን የታሪክ ጠባሳ ሲጥል ፡

ለ/ አሁንም በቤተ-ክርስቲያናችን ቅዱስ ሲኖዶስ በተባለዉ ስብሰባ ላይ የብጹአን አባቶችን አፍ ለማዘጋት ሚልተሪዎች የዓለም ሰዎች ያዉም የደም አፍሳሹ እነአቦይ ጸሃዬ በሲኖዶስ ስብሰቢነት በሊቃነ ጳጳስቱ ወነበር ላይ መቀመጣቸዉ ኦርቶዶክሳዉያንን አሳዝኖናል ፡፡ ይህአይነት ድርጊት ተደረጎ አያዉቅም ነለገሩ የህገ ወጡ ሲኖዶስ ጀርባ በጊዜዉ ተገልጧል የነአባ ገብረ መድህን ማንነትም ፍንትዉ አድርጎ አሳይቶናል

ሐ/ በቤተ-ክርስቲያናችን አዉደ ምሕረት ላይ ደም ያፈሰሰ መለኩሴ ጳጳስ የለም እሳቸዉ ግን በቤተ ክርስቲያናችን አዉደ ምሕረት በፊታቸዉ በጥይት አስገድለዋል በቤተ-ክርስቲያንን ምእመናን ከቅጥረ ቤተ-ክርስቲያን አስዎጥተዉ አሳልፈዉ በመስጠት ለወያኔ አጋዚ ጥይት ሲሳይ አድርገዋል፡፡

መ/ ፡-ዘፋኝነትን የምትቃወም ቤተ-ክርስቲያን በግብሯ ዓለማዊ የሆነችን ሴት ቢዮነሴን በተቀበሉበት ወቅት አምልኮተ እግዚአብሔር የምናከናዉንባቸዉን ንዋየ ቅድሳት በማስወጣት ቤተ መቅደሳችንና ታቦተ ህጉን በማቃለል ለመናፍቃ መሳቂያ አድርገዋል ፡የክርስቶስ ስጋና ደም የሚፈተትባትን ቤተ-ክርስቲያን አቃለዋል፡፡

ሠ/ የቤተ-ክርስቲያናችን የክህነት ማዕረግ ጫፍ የሆነዉን የጵጵስና መዐርግም ለረባ ላረባዉ በጉቦ በዘር በፖለቲካ በመስጠት ቤተ-ክርስቲያኗን አስነቅፈዋል የሚያሳፍረዉ ለደርግ ወታደር እንኳን ሳይቀር ሰጥተዋል እንዲህ ያደርገ የሐይማኖት መሪ ከእሳቸዉ በቀር አንድም የለም ለዚህም ነዉ ከጥንቱ ፈተና ይልቅ የዛሬዉ የነአባ ገብረ መድህን /አባ ጳዉሎስ/ የዉስጥ ፈተና አይነቱና ይዘቱ የሚያሳፍር አዲስ ክስተት በመሆኑ ለየት የሚያደርገዉ፡፡

2/ ጸሐፊዎቹ በመግለጫችን ተራ ቁጥር 1 ላይ ያለዉን « በሐይማኖታችንና በብጹአን አባቶቻችን ላይ እየተቃጣ ያለዉ አባገነናዊ ትንኮሳ እንዲሁም በእግዚአብሐር የተቀቡትን አባቶች የስም ማጥፋት ዘመቻ ይቁም ያልነዉን » ይህን ካላችሁ በእግዚአብሔር የተቀቡትን አባቶቻችን ለምን አታከብሩም ያለያ ማንነታችሁን ለዩ በማለት የዘለፋ መግለጫ አስቀምጠዋል፡፡

ወዳጅ መቸም ግብራቸዉን የማያዉቅ ያልሰማ ያላየ ሰዉ ኑሮ አባ ገብረ መድህን ህጋዊና መንፈሳዊ የእግዚአብሐር ሰዉ ናቸዉ ብለን አንቀበልም እደዚሁም በፈቃደ እግዚአብሔር ሳይሆን በፈቃደ ወያኔ የተቀቡትን ስርአቱ የማይፈቅድላቸዉ የደርግ ወታደር የነበሩትን አስማማው አባ ያዕቆብንም የሐይማኖት አባት ብለን ልንቀበል አንችልም ምክንያቱም የቤተ- ክርስቲያናችን ሕግ አይፈቅድምና ፡፡
መጽሳፉን ማንበቡ ነዉ የሚሻላችሁ ህግና ስርአታችን ማፍረስ የለመደዉ የወያኔዉ ጳጳስ አባ ገብረ መድህን እስኪ ማን ይሙት ምንም የቤተ-ክርስቲያኗን ትምህርት የማያዉቁትን ድን ጸመ ድን አቋቋም ዜማ ቅዳሴ ብሉይ ኪዳን ሐዲስ ኪዳን ቅኔ ያልተማሩትን በወጉ ቀድሰው እንኳ የምያቀርቡትን የደርግ ወታደር ጳጳስ ሲያደርግ ሕጉ ቢፈቅድማ ኖሮ ስንቱ ሊቃዉንት የቤተ-ክርስቲያኒቱ ልጆች በደርግ ግዳጅ ዘምተዉ ከዉትደድርና የተመለሱ ሊቃዉንት ወንድሞቻችንና አባቶቻችን ነበሩ አደል? ዳሩ ግን አባ ያእቆብ የተባሉት የደርግ ወታደር የተሾሙት በፖለቲካ በመሆኑ ለቤተ-ክርስቲያናችን ታሪክ ፈተና ሆነ፡፡

3/ ጸሐፊዎቹ በመልስ ጽሑፋቸዉ ተራ ቁጥር 4 ሐ ላይ አባ ያዕቀብ የተባሉት አባታቸዉ የኋላ ታሪክ ሌላ ስለሆነ «ወታደር የነበረን ሰዉ ክርስቶስ አይፈልገዉም የሚል ትምህርት በመጽሐፍ አይገኝም ካሉ በኋላ ሐዋርያት ከምን እንደተመረጡ ለሚያዉቅ ክርስቲያንም ወታደር የነበረን ሰዉ ክርስቶስ አይወደዉም ብሎ መናገር አላዋቂነት ነዉ ብለዋል» እኛ ወታደር የነበረን ሰዉ ክርስቶስ አይፈልገዉም ወይም አይወደዉም አላልንም፡፡ ክርስቶስ እንዲሁ የሰዉን ልጅ በሙሉ በባዶ እንዲሁ ወዷልና ዮሐ 3 16 ሮሜ 5 6-9 ግን ሁሉም መሪ ሊሆኑ አልተመረጡም የቤተ ክርስቲናችን ህጉ አይፈቅድም ጭራሽ ጳጳስ መሆን አይገባም አይፈቅድምም ነዉ ያልነዉ፡ በምንም ይሁን በምን ተሰማርቶ ኃጢአተኛ ሆኖ ኑሮ ባኋላ ንስሐ የገባ ጵጵስና አይሾምም ፍትሐ ነገስት ፳፡ረስጣ ፸፩ አንድ ሰዉ ሳይገባዉ ኤጲስ ቆጶስ የሚሾም ቢኖር ይለይ ፍት መ ፳ ፻፸፯ የሐዋ ሥራ ፰ ፲፰፡ ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን እደራሴነት ማዕርግ በፖለተካ ሳይሆን ስርዓተ ቤተ-ክርስቲያን ለሚፈቅድላቸዉ ሊቃዉንት መነኮሳት ይሁን ነዉ ያልነዉ፡፡በሀገራችን ቁጥራቸዉ የበዛ ሊቃዉንት መነኮሳት ንጽኅናን ከእዉቀት ቅድስናን ከስርአትጋር አሟልተዉ የያዙ መቸ ጠፉ? ለሚገባቸዉ ህገ ቤተክርስቲያን ፈቅዶላቸዉ በፖለቲካ ሳይሆን በፈቃደ እግዚአብሔር ለሚመረጡት ይሁን ነዉ ያልነዉ፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ሐዋርያዉ ቅዱስ ጳዉሎስ ሮሜ 2፡12 ሕግ ተሰርቶላቸዉ ሳለ ከህግ ወጥተዉ የበደሉ ሰዎች ፍርዳቸዉ ከመጠን በላይ ነዉ ብሏልና ፡፡ ደግሞም ሐዋርያትን ከዉትድርና

መረጣቸዉ የሚልም የለም አልመረጠምም ::እንዲሁ መፅሐፉን እንደስጋ ሀሳብ አትተርጉሙት የአባቶቻችን ስርዐትም አታጣሙት ባጠቃላይ አቡነ ያዕቆብ (ወታደር አስማማው) ለጵጵስና ህጉ አይፈቅድላቸዉም ::
**በዚህ አይነትማ አቶ አባይ ጸሐዬ ትናንት ሲኖዶሱን ስለሰበሰቡና ሰላዋያዩ ነገ እሳቸዉም ጳጳስ ሊሆኑ ነዋ ማለት ነዉ ?--- ፳፫ ረስጣ ፳፭ ----ሕጉ ስለማያዝ አያስኬድም** ባጠቃላይ ሊቃዉንተ ቤተ ክርስቲያንንና ምዕመናንን ያሳፈረ ጉዳይ ነዉ ለዚህም ይመስላል ሰዉየዉ በዚህ እኛ ባለንበት ሳዉዝ አፍሪካ ተሰዉረዉ የፖለቲካ ስራቸዉን የሚያራምዱት ::

4/ ጸሐፊዎቹ በመግለጫ ተራ ቁጥር 2 ላይ ያሰፈርነዉን በመጥቀስ ሕጋዊ የሆነዉን ሲኖዶስ መግለፃችን ጠቅሰዉ ህጋዊ ያልሆነ አለ እዴ? በማለት ጠይቀዋል ቀጥለዉም ሲኖዶስ ማለት የመሰብስሰቢያ አደራሹና ፓትርያርኩን ብቻ የሚወክል ሳሆን ብጹአን አባቶችንም አጠቃሎ የያዘ ነዉ እንጂ ሲሉም ደምድመዋል:: ወዳጀ ሲኖዶስ ማለት በፓትርያርክ የሚመራ የጳጳሳት ጉባዔ ማለት ነዉ ፍት ፬ ፵፱ ያለፓትርያርኩ ሲኖዶስ ሊኖር አይችልም ያለ ጳጳሳትም ሲኖዶስ አይኖርም ::ፓትርያርኩ ቢሰደድ እንኳን በአቃቤ መንበር እየተመራ መንበሩ ግን ጾንታ ትጠበቅ ይላል እንጅ :: ፍት -፬፥-፳ ፤ ፬ ፵፱ **ፓትርያርክ በህይወት እያለ ሌላ ፓትርያርክ አይሾምም::**

ዳሩ ግን የቤተ ክርስቲያን ህግና ስርአት አላዉቅም አላከብርም ባለ ህገ ወጥ ካድሬ ተስፈኞች ለጥቅም የተገዙ በመሆኑ ካልተረዱ በቀር ሕገ ወጥ የሆነን አካል አባ ገብረ መድህንና መሰሎቹን ህግ አስከብርልን አላልንም ያስቀመጣቸዉን አካል ግን በመጀመሪያው መግለጫችን ቁ 6 ላይ ከቤተ ክርስቲያናችን እጁን እንዲያነሳና እንዲቆጠብ ስለቤተ ክርስቲያናችን ካድሬህን አንሳ ከግፍ ተቆጠብ አትለያየን ጣልቃ አትግባብን ብለናል:: **ነገር ግን በአንጃዎች ቅኝ ግዛት ጭቆና ጊዜዉ እስኪያልፍ በጸሎት የሚጠብቁት አባቶች በየክፍለ ሀገሩና ሀገረ ስብከታቸው ተመድበዉ ሕዝባቸዉን የሚያገለጉሉትን ብጹአን አረጋዉያን አባቶቻችን አላችሁም አላለችሁም አንቃወምም እንወዳቸዋለን እናከብራቸዋለንም**::ይልቁንም ከተሰደዱት ብጹአን አባቶች ጋር በስጋ ቢለያዩም በመንፈስ አንድ ሆነዉ በጸሎታቸዉና በስራቸዉ ጠንክረዉ የቤተ ክርስቲያናችንን አንድነትና ፍቅር ይመልሱልን ዘንድ ጠየቅናቸዉ እንጂ ባንዳዎችን አላልንም ::
እነዚህን ብርቅ የቤተ ክርስቲን አባቶቸ ከወታደሮችጋርም ልናነጻጽራቸዉ አንችልም፤ይልቁንም የሰነፍ መመለሻዉ እሩቅ ነዉና እናንተዉ አድርጉት::
ጊዜዉ እስኪፈታዉ የብጹአን አባቶቻችንም ስም ከነ ሙያቸዉ ብንገልጸዉ ጥሩ በሆነ ነበር ግን ለናንተና ለወያኔ ማስጠቆርና ለብቀላ ሰለባ ማድረግ ሰለሆነ ትተነዋል::

5/ ጸሐፊዎቹ በነሱ በመገለጫቸዉ (በመልሳቸው) 4-ለ ላይ አባ ያዕቆብ ስለተባሉት ስለወታደር አስማማዉ የተሸሙበትን ምክንያት በጉቦ ወይም በዝምድና ነዉ ብላችኋል በማለት አስተባብለዋል:: ነገሩ እንዲህ ነዉ የመግለጫችን ጽሑፍ ላነበበ እኛ ያልነዉን ባይስተዉም እነሱ ግን በማቴዎስ 23:24 እናንተ እዉሮች ትንኝ ትንሹን የምታጠሩ ግመልን ግመሉን የምትዉጡ እንደተባለ በየዋህነት የሚከተሏችሁን ምእመናን እንዳይንቁባችሁ ዲያብሎስን በልባችሁ አንግሳችሁ ለፍርድ የምትርቁ ቢመስላችሁም አታመልጡም ዳሩግን እኛ ያልነዉ አባ ገብረ መድህን /አባ ጳዉሎስ/ ስልጣን የሚሰጡት በጉቦ በዝድናና:በዘር በፖለቲካ ነዉ ሰንል በመጨረሻዉ 2ኛ አንቀጻችን ላይ በግልጽ ጠቅሰን በዚህም በሳዉዝ አፍሪካ የተቀመጡትም የደርግ ባህር ኃይል ወታደር አስማማዉ /አባ ያእቆብ/ የተሾመዉ የወያኔዉ ገ/መድህን የድርጅት አባል በመሆናቸዉ ወያኔ ለራሱ ፖለቲካ ያስቀመጣቸዉ መሆኑን **በፖለተካ ነዉ ብለን አረጋግጠናል**::አዉቆ የተደበቀ ቢጠሩት አይሰማም ነዉና እዉነቱን ስለምትደብቁ ነዉ እኩይ ታሪካቸዉን ደብቀዉ ለማስመሰል ያልተጻፈ አንብበዉ ዙሪያዉን የሚዞሩት::

<u>ወዳጄ በፖለቲካ ነዉ የተሾሙት ብለን</u> በግልጽ ያስቀመጥነዉን ትተዉ በጽሑፋቸዉ ሌላዉን ያልተፃፈ አንብበዉ ዙሪያዉን የምትዞሩ በፖለቲካ የሚለዉ በእሾህ ነዉ በብረት የታጠረባችሁ? ደጋግሞ ያልታያቸዉ ቁስል ያለበት አያስነካም ሆኖ ነዉ እንጂ:
6/ ሌላዉ የሚያሳፍረዉ ጸሐፊዎቹ በመጨረሻዎቹ አንቀጻቸዉ ላይ <u>በዚህ በሳዉዝ አፍሪካ ያለዉን ሕዝብ፤ በየክፍለ ሀገሩ ያለዉን ምዕመናን ሀገር ቤት እያለ በአመት አንድ ጊዜ</u> **እንኳን የማገኘዉን አባታዊ ቡራኬ አሁን በአባ ያእቆብ /በወታደሩ/ አግኝቷል በማለት ዉሸትና ድፍረት በሞላበት ሁኔታ አስፍረዋል ::ይህም ዉሸታቸዉ በደቡብ አፍሪካ የምንገኝ አርቶዶክሳዉያንን በሙሉ አሳዝኖናል :: <u>እዉን በኢትዮጵያ እለት እለት የማይገኝ ቡራኬ በሳዉዝ አፍሪካ ተገኘ ብሎ ማለት ሙሉ በሙሉ ዉሸት ከመሆኑም በላይ በሀገር ቤት ያሉ አባቶችም ምንም አባታዊ ቡራኬ አይሰጡም እንደማለት ይቆጠራል:: ይህ ደግሞ በእዉነት ከባድ ድፍረት ነዉ በጣም ያሳዝናል</u>** ::ይህን የጻፉ ሰዎች ቆይተዉ የተጠመቃችሁም/ክርስትና/ የተነሳችሁም ከዚህ ሳዉዝ አፍሪካ መጥታቸሁ በኛ ነዉ እንዳይሉን እንጂ::ክህነትን በጠዋት ይዘዉ በእግዚአብሔር የተመረጡ ለአገልግሎት የተጉ በቤ-ክርስቲያንችን ትምህርት ሙሉ የሆኑ መጻሕፍትን ከነትርጓሜዉ ሰንቀዉ የያዙ በሐይማኖትና በንጽህና ተጠብቀዉ የሚኖሩ ከብጹዐን አባቶች ሊቃነ ጳጳሳት እስከ ቀሳዉስት ድረስ በተትረፈረፈባት ሀገርና በምትፈለፍለዉ ቤተ-ክርስቲያን በኢትዮጵያ ዉስጥ ቡራኬ የለም: በአመት አንድ ጊዜም አግኝተን አናውቅም ማለት ይህ የዲያብሎስ ስራ ስለሆነ ያሳፍራል ሊቃዉንተ ቤተ-ክርስቲያን

አባቶችንም መናቅ ነዉ፡፡ዳሩ ግን«ወንጌል ከሰበረዉ ፖለቲካ ያሰከረዉ »የተባለዉ እንደነሱ ላሉት አይደል ራሱን ለእግዚአብሐር ሳይሆን ለጥቅም ብቻ ካስገዛ ሰዉ ምን ጥሩ ነገር ይጠበቃል፡፡

**እንግዲህ አባ ያዕቆብ የተባሉት ወታደር የኢሠፓን መለዮ ሚሊተሪ ቆብ ባጠለቁበት እራሳቸዉ እድሜ ለወያኔ የብጹአን አባቶቻችን አስኬማ ደፍተዉበት አየን :የጦር መሳሪያ ክላሺ በያዙበት እጃቸዉ የብጹአን አባቶቻችን በትረሙሴ በድፍረት አይገባኝም ሳይሉ ከያዙ ሰዉና ከሚከተል አንጃና ካደሬ በአትዮጵያ አባትም ቡራኬም የለም ቢል ምን ይደንቃል፡፡**ይለቁንም ጸሐፍዉ ማንነትህን በዉል ስለምናዉቀዉ የብዕር ስም ተጠቅሞ የዋህ ምዕመናንን በማጭበርበር ወደ ከፋ ስህተት አታቅና ደግሞ በደንብ እየተዋወቅን ራስን የሌለ ጉባዔ ጠቅሶ ማወናበዱ አይጠቅምም በመጽሐፍ ሌላ ያመስግንህ እንጅ አፍህ አይደለም «ድንጋይ ከባድ ነዉ አሸዋም ሸክሙ ጽኑ ነዉ ተብሏልና»

7/ ጸሐፊዉ በተራ ቁጥር 3 ኦና በመጨረሻዉ አንቀጽ ላይ ስለ ወያኔዉ አባ ያእቆብና የኢባሲዉን ሴራ በተመለከተ የጠቆምነዉን ነገርና በይደር የስተላለፍነዉን መልእክት በመቃወም እዉነት እንዳልሆነ ለመቀበልና ላለመቀበል መረጃ ይጎድለዋል በማለት አያይዘዉም **ቢሆን እንኳን ለምን ይገለጣል** የሚል መልዕክት አስቀምጠዋል ፡፡የቤተ ክርስቲያን መፍረስና መጥፋት ያላስጨነቃቸዉ ህሊና የማይወቅሳቸዉ ሰዎች የሥጋ ሀሳባቸዉ ስለተነካና ወያኔዉን ሐዋርያቸዉን ያስር አለቃ አስማማዉ ምስጢር እንዳይገለጥባቸዉና ሕዝቡ እንዳዉቅባቸዉ የካምን ታሪክ አንስተዉ የማይመሳሰል ተግሳጽ አይሉት ልመና ተመጻድቀዋል ፡፡

እኛ ግን ቤተ-ክርስቲያናችን ወደ አላስፈላጊ መንገድ እየተመራችና ሊቃዉንት እየተሰደዱ የመናፍቃን መሳለቂያ ስትሆን ወያኔም እንዳሻዉ የነፍጠኞች ዋሻ ብሎ ቤተ-ክርስቲያናችን ሲሰድብ ሲያሻዉ ደግሞ እንደነ አባ ያእቆብ ያሉትን መልምሎ ፖለቲካዉን ሲያራምድባት እያየን ያላወቁት ምእመናን ችግሩን ከሐይማኖት ጋር እገናኝተዉ ተሳስተዉ እንዳይጠፉ ምክንያቱና ጥፋቱ የትጋ እንደሆነ የምናዉቀዉን እንጠቁማለን ፡ ያልያ ግን በመሸፋፈን ካለፍነዉ አድሮ መልኩን ቀይሮ ለቤተ- ክርስቲያን ከዚህ የከፋ አደጋ ይሆናል፡፡ **<u>ጸሐፊዉ በመጨረሻዉ«ይህን ስንል በቤተ-ክርስቲያን ዉስጥ ችግር እንዳለና ሲኖዶሱም በፍጹም ስራዉን በሰላም እየሰራ እንዳልሆነ ሊሰመርበት ይገባል በማለት »በተምታታ ሁኔታ የጻፉትን ሁሉ የሀሰት መልሳቸዉን አፍርሰዉታል</u>** ፡፡ባጠቃላይ አቡነ ያዕቆብ ማን ናቸዉ? ከየትኛዉ ክፍለ ጦር ነበሩ? የት አካባቢ ስንተኛ ብርጌድ? ከደርግ ሰራዊት እንዴት ወጡ? እንዴት ወደ ቤተ-ክርስቲያን ቀረቡ? ስልጣነ ክህነትን ዲቁና ማዕረግ ማን ሰጣቸዉ በማን መነኮሱ መቾ መነኮሱ መቀሌ ተመድበዉ አልነበር ለምን ተነሱ? በምን ምክንያት በኋላ ጵጵስና ማዕረግ ያለህገ ቤተ-ክርስቲያን እንዴት ተሸሙ? ለጵጵስና ሲቀርቡ ሲኖዶሱ ምላአተ ጉባኤ አምኖበታል ወይ? የተቃወሙትስ ምን ተባሉ? በህገ ወጥ ከተሾሙ በኋላ እንዴት ሳውዝ አፍሪካ ተመደቡ? በዚህ የሚገኘውን የኢትዮ- ኮሚዩኒቲ ለማፍረስ ምን ታቅዶ ነበር? ወታደር አስማማው (አባ ያዕቆብ) በሳዉዝ አፈሪካ ከኢምባሲው ጋር የፖለቲካ እንቅስቃሴያቸዉ ምን ይመስላል? ከኢምባሲው ሰራተኞች ጋር መቼ መቼ ለሪፖርት ይገናኛሉ? ለዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና ለአባ ጳዉሎስ የጻፉትን ደብዳቤ 1 ሰነድ በእጃችን ስለገባ እሱን ጨምረን በአጭሩ በጥሩ ሁኔታ አዘጋጅተን ወያኔ ምን ያህል የጥፋት ስትራቴጅዉን እንደዘረጋብን በሶስተኛው ክፍል እናቀርባለን ሠላመ እግዚአብሔር ሀገራችንና ሀይማኖታችንን ይጠብቀልን የድንግል ማርያም የቅዱሳኑ በረከት አይለየን ወስባሀት ለእግዚአብሔር፡፡

**ይቀጥላል**፡፡→→